# አብዮታዊት ኢትዮጵያ

15



የታጠቀን ጠላት ለመቋቋም የጭቁን ሴቶች መታጠቅ አስፈላጊ ነው ።

ኅዳር ፴ — ፲፱፻፸፱ ዓ. ም.

**ለውይይት መነሻ**

**አብዮታዊት ኢትዮጵያ ከቁጥር ፩ ጀምራ «ለነማርክስ ፍልስፍና አጭር መግቢያ» በሚል ርእስ ሥር በተከታታይ ትምህርታዊ የሆኑ የፍልስፍና ጽሑፎች ታቀርባለች ። እነዚህ ጽሑፎች የማርክሲዝምን ርእዮተ ዓለም ገና ለመጀመሪያ ጊዜ ለሚተዋወቁ የውይይት ክበቦች መነሻ ሃሳቦች እንደሚሰጡ ሆነው የቀረቡ ናቸው።**

# የሕብረተሰብ መሠረትና ልባስ

## ፲፩ኛ ትምህርት ከን - ዓ

እስካሁን ድረስ የኅብረተሰቦችን ዕድገትና የዘመናት መለዋወጥ የተመለከትነው የኢኮኖሚውን መለዋወጥና የሰዎችን የኑሮ ሁኔታ መሻሻል እየተከተልን ነበር ። የሕብረተሰቦችን ዕድገት ከስልተምርቶች መለዋወጥ አንፃር እያየነው መጥተናል ። ግን ከነዚህ ጋር አብሮ የተለወጠ ሌላ ብዙ ነገር አለ ። የዘመኑ ሰው የሚያስበው እንደጥንቱ ሰው አይደለም ። የኅብረተሰቦች መሠረት እየተለዋወጠ የሄደውን ያህል ሃይማኖቶች ፤ ፍልስፍናዎች ፤ የመንግሥት ዓይነቶች ፤ ባህሎች . . . ሁሉ እየተለዋወጡ ሄደዋል ።

ጥያቄው እንግዲህ በነዚህ በሁለቱ ማለትም በኅብረተሰቡ ስልተምርትና በሃይማኖት በመንግሥት መለዋወጥ መሀከል ግንኙነት አለ ወይ ? የሚለው ነው ። ማርክሲዝም በሁለቱ መሀከል ግንኙነት አለ ይላል ። ሁለቱ እየተጋገዙና እርስ በእርስ እየታገሉ ወደፊት ይራመዳሉ በባርያ ሥርዓት ውስጥ ለምሳሌ የሰው ልጅ መሸጡ ፤ መለወጡ ትክክለኛ ነገር መስሎ ይታይና ይታመንበት ነበር ። የኅብረተሰቡ የምርት ኃይሎች ተሻሽለው የባርነት የኢኮኖሚ መሠረት ሲናጋ ባርነትን የሚያጸድቀው እምነትም ፤ ባርነትን አጽድቆ በሕግ የደነገገው ሥርዓት መንግሥትም አብሮ ተናጋ ። ቀድሞ አሜን ብሎ ተቀብሎ የነበረው ባርያ «እምቢ» የሚል አስተሳሰብ ከመቼውም ይበልጥ ተቀረጸበት ። አመጸ ። የፊውዳልም ሥርዓት—ኢኮኖሚ ሲናጋ እንደዚሁ በሐሳብ በፍልስፍና ደረጃ ታላቅ ለውጥ ተደርጓል ። ዛሬ በኢትዮጵያ ፊውዳሊዝምንና ኢምፔሪያሊዝምን ደምስሰን አዲስ ሕዝባዊ ሥርዓት ለመገንባት በመታገል ላይ ነን ። ከመቼውም ይልቅ በሕዝቡ መንፈስ የብዝበዛ ጥላቻ ፤ የመሳፍንት ጥላቻ ፤ የአዲስ ኑሮ ጉጉት አድሮበት ለነዚሁ ዓላማዎች ተሰልፎ ሲታገል እናየዋለን ። በቀድሞው ጊዜ ስነጽሑፉ ፤ ፍልስፍናው ሙዚቃው ፤ ጠቅላላው የሰው አስተሳሰብ ፊውዳሊዝምንና ኢምፔሪያሊዝምን የሚቀበለውን ያህል ዛሬ ፀረ ፊውዳልና ፀረ ኢምፔሪያሊስት አስተሳሰብ በሀገራችን እጅግ እየተስፋፋ ነው ። በዚህ አንፃር ደግሞ የፊውዳሉን ሥርዓት የኢኮኖሚ መሠረት የሚያናጉና የሚደመስሱ የኢምፔሪያሊዝምን ተጽእኖ በኢትዮጵያ የሚቀንሱ ዓዋጆች ከሥራ ላይ በመዋል ላይ ናቸው።

እንግዲህ በሁለቱ መሀከል የጠበቀ ግንኙነት እንዳለ ግልጽ ነው ። ግን ማን ነው ማንን የማያንቀሳቅሰው ? ማነው በቅድሚያ የሚለወጠው ? የሰዎች አስተሳሰብ ስለተለወጠ ነው የፊውዳሊዝም ኢኮኖሚ የተደመሰሰው ወይንስ የፊውዳል ኢኮኖሚ ስለተደመሰሰ ነው የሰዎች አስተሳሰብ ፀረ ፊውዳል የሆነው ?

ከዚህ በፊት እንዳልነው የኅብረተሰቦች ዋና አንቀሳቃሽ ኃይል የስልተምርቶች እንቅስቃሴ ነው የአንድ ሀገር ስልተምርት እንዴት የተቀሩትን ሕብረተሰብ ነክ የሆኑ ጉዳዮች ማለትም ሕጉን ፤ የመንግሥቱን ዓይነት ፤ ባህሉን ፤ ፍልስፍናውን እንደሚወስናቸው ማየት ያስፈልጋል ። በሁለቱ መሀከል ያለው ግንኙነት ርግጥ የተወሳሰበ በመሆኑ እነዚህ የጠቀስናቸው ኅብረተሰብ ነክ ነገሮች እንዴት መልሰው በስልተምርቱ ላይ ተጽእኖ እንደሚያደርጉ ማየት ይጠቅማል ። የነማርክስ ፍልስፍና ይህንን ጉዳይ «መሠረትና ልባስ ወይም (ቤዝ) ሱፐርስትራክቸር» በሚለው ቴዎሪ ሊያጠና ይሞክራል ።

በአንድ ኅብረተሰብ ውስጥ በሰዎች መካከል በሚሊዮን የሚቆጠሩ የግንኙነት ዓይነቶች አሉ ።

በሕግ የተደነገጉ ግንኙነቶች አሉ ። በሥራ ቦታ የሚደረጉ ግንኙነቶች አሉ ። ለምሳሌ በሠሪና በአሠሪ መሀከል ።

የአንድ ኅብረተሰብ የምርት ኃይሎች በሰዎች መሀከል የሚኖሩትን የምርት ግንኙነቶች ይወስናሉ ብለናል ። ማለትም የኅብረተሰቡን የኢኮኖሚ መዋቅር ይወስናሉ ። እነዚህ የምርት ግንኙነቶች ደግሞ በተራቸው በኅብረተሰቡ ውስጥ ባሉት ሌሎች በሰዎች መካከል የሚደረጉ ግንኙነቶች ላይ ከፍ ያለ ተጽዕኖ አላቸው ። እንዲያውም በኅብረተሰቡ ውስጥ የሚገኙት አስተሳሰቦች ፤ እምነቶች ፤ ድርጅቶች ተመስርተው የሚቆሙት በዚህ የኢኮኖሚ መዋቅር ላይ ነው ። በሕብረተሰቡ ውስጥ ያሉ ሐሳቦችና እምነቶች የፖለቲካ ፤ የሕግ ነክ ፤ ፍልስፍና ሃይማኖት እንደዚሁም ንቅናቄዎችና ድርጅቶች ማለትም መንግሥት ፤ ቤተክህነት ፤ መስጊድ ፤ የፖለቲካ ፓርቲዎች . . . በአንድ በተወሰነ የኢኮኖሚ መዋቅር ላይ የሚበቅሉ ናቸው ።

የምርት ግንኙነቶች የሚወሰኑት የምርት ኃይሎች በደረሱበት ደረጃ ነው ። ግን ደግሞ የምርት ግንኙነቶች በጠቅላላው በኅብረተሰቡ ያሉትን ሌሎች ግንኙነቶች ሁሉ ይወስናሉ ። ይህንን ሀቅ በማብራራት የነማርክስ ፍልስፍና መሠረትና ልባስ ወይም «ቤዝና ሱፐርስትራክቸር» በሚለው ቴዎሪ ይጠቀማል ። ይህ ቴዎሪ የአንድን ኅብረተሰብ ሕይወት የሚመለከቱ ጉዳዮች ሁሉ እንዴት ዞረው ዞረው ከስልተምርቱ ጋር የተያያዙ መሆናቸውን የሚያስረዳ ቴዎሪ ነው ።

ማንኛውም ኅብረተሰብ የራሱ የሆነ የኢኮኖሚ መሠረትና በሱ ላይ የተገነባ ልባስ አለው። እዚህ ላይ የኅብረተሰብ መሠረት የምንለው ምንድን ነው ? ልባስ የምንለውስ ? መሠረት ማለት ኅብረተሰቡ የቆመበት የኢኮኖሚ መዋቅር ሲሆን ልባስ የምንለው ደግሞ በዚህ የኢኮኖሚ መዋቅር ላይ ተቆርቁሮ የሚገነባውንና በኅብረተሰቡ የሚታየው አስተሳሰብ ፤ ሕግ ፍልስፍና ፤ ሞራል ፤ ሥነ ጥበብ ፤ ሃይማኖትና ከነዚህም ጋር የተያያዙ ድርጅቶች ማለትም ፓርቲዎች ፤ መንግሥት ፤ ቤተ ክህነት ወይም መስጊድ የመሳሰሉትን የሚያጠቃልል ፅንሰ ሐሳብ ነው ።

ለአንድ ኅብረተሰብ መሠረት የሚስማማ ፍልስፍና ለሌላው በፍጹም አይሆነውም ። ለምሳሌ በባርያ ኢኮኖሚ ላይ ወይም በፊውዳል ኢኮኖሚ ላይ በተመሠረተው ኅብረተሰብ ውስጥ « ሰው ሁሉ እኩል ነው » የሚለው ፍልስፍና ተቀባይነት የለውም ። በዚህ አንፃር ለምሳሌ በባርያው ሥርዓት ውስጥ ባርያው እንኳን እኩልነት ይቅርና ሰው መሆኑ ጥያቄ ውስጥ ስለማይገባ « የሚናገር ከብት» እየተባለ ነበር የሚቆጠረው ። በፊውዳል ሥርዓት ውስጥ ደግሞ «ጭዋ» «ባለጌ» እየተባለ ሰው የበላይና የበታች እየሆነ ይቀርባል ። በእንዲህ ዓይነት መሠረቶች ላይ የቆሙ ሕብረተሰቦች ውስጥ እንግዲህ የመንግሥቱን ዓይነት የወሰድን እንደሆነ የገዥ መደቦች በመሰላቸው ለጥቅማቸው ያቆሙት አገዛዝ እንደሆነ እንጂ በጠቅላላው ሕዝቡ ነፃ ምርጫ ላይ የተመሠረተ መንግሥት ሊሆን አይችልም ነበር ማለት ነው ። ይህ ባርያውንና ጢሰኛውን ከመንግሥት ሥልጣን ጉዳይ በሕግ አግዶ የያዘ ሥርዓት በኢኮኖሚውም ደረጃ ባርያውም ጢሰኛው በሕግ ዝቅተኝነታቸው ታውቆ እየተገደዱ ለአሳዳሪያቸው የሚሠሩበት ሥርዓት ነው ። ግልጽ ጭቆና ግልጽ ብዝበዛ ዓይን ያወጣ በበላይነትና በበታችነት የተመሠረተ መንግሥት ነው ።

በካፒታሊስት ሥርዓት የሄድን እንደሆነ ደግሞ እንደዚሁ የመሠረቱንና የልባሱን ግንኙነት እናያለን ። የካፒታሊስት ብዝበዛ እጅግ በረቀቀ ዘዴ ነው ። ወዝአደሩን እንዲያውም ረሀብ ያስገድደዋል እንጂ ተቀጥሮ እንዲሠራ ፤ የሚያስገድደው ሕግ የለም ። ስውር ብዝበዛ ነው ። በፖለቲካውም በኩል ጭቆናው ስውር ነው ። «ነፃነት እኩልነት አንድነት» በሚለው መፈክር ስር ተሸፍኖ የሚደረግ ጭቆና ነው ።

ባጭሩ በዚህ ምሳሌ እንደምናየው መሠረትና ልባስ የተያያዙ ናቸው ። ይህ ደግሞ በነፃነትና በመንግሥት ጉዳይ ብቻ ሳይሆን ከዚህ ሁሉ ጋር በጥብቅ በተያያዙት በፍልስፍና ፤ በስነጽሑፍ በሞራል . . . ወዘተ የሚታይ ግንኙነት ነው ። እነዚህ ሁሉ ከሕብረተሰቡ መሠረት የፈለቁ ከሰው ጋር የተያያዙ ናቸው ። ሞራል ከሕብረተሰቡ ኢኮኖሚ ሁኔታ ጋር የተያያዘ በመሆኑ አንዲት በጣም ቀላል የሆነች ምሳሌ እናሳይ ።

«አትግደል» የምትለዋን ሕግ እንውሰድ ፤ ይህ ሕግ ከመውጣቱ በፊት ሰዎች የግድያን ድርጊት እንዴት ይመለከቱ ነበር ? በጋርዮሽ ዘመን እንዳየነው ሰው ከዕለት ጉርሱ በላይ የሚያተርፈው ነገር የለውም ነበር ። ስለዚህ በጐረቤት ጐሣዎች መሀከል ጦርነት ተደርጐ ሰው ሲማረክ እሱን በእስረኝነት «አንከባክቦ» መቀለቡ ጨርሶ የማይቻል ነገር ነበር ። ስለዚህ እስረኛን መግደል እንዲያውም አንዳንድ ጊዜ መብላት ማንም የተቀበለው ነገር ነበር ። በዚያን ጊዜ በነበረው ኢኮኖሚ እንግዲህ « አትግደል » ብሎ መግደልን መጥፎ ነገር አድርጐ መቅረብ ጨርሶ ኅብረተሰቡ የማይቀበለው ሞራል ነበር ማለት ነው ። በኋላስ « መግደል » እንዴት በመጥፎ ዓይን ለመታየትና እስካሁን ሊወርድ ቻለ ። ሰው ለሰው « ለመራራትና » መስሎቹን መግደል ሞራሉ የማይቀበለው ነገር ለመሆን የበቃው እንዴት ነው ? ይህ የሆነው የኅብረተሰቡ ኢኮኖሚ እየተለወጠ ሄዶ የሰው ጉልበት ከዕለት ጉርስ በላይ ማምረት በቻለበት ጊዜ አንድን ሰው ከመግደል ይልቅ ባርያ አድርጐ ማሠራቱ ይበልጥ ጥቅም የሚሰጥበት የኢኮኖሚ መሠረት እየተጣለ በሄደበት ወቅት ነው ።

ባጭሩ እንግዲህ የሕብረተሰብ መሠረት ሲለወጥ ልባሱም (የመንግሥቱ ዓይነት ፤ ሕጉ፤ሞራሉ ፍልስፍናው . . . ወዘተ) ሁሉ አብሮ ይለወጣል ማለት ነው ። ይህ ልባስ ከመሠረቱ ከኢኮኖሚው ጋር ያለው ግንኙነት ከሁለት አንፃር ሊታይ ይቻላል ። መሠረቱ በብዝበዛ ላይ የተመሠረተ ሕብረተሰብ ከሆነ የመደቦች ትግል አለ ማለት ነው ። ስለዚህ በልባሱም ደረጃ በመንግሥት ዓይነት ፤ በሕጉ ፤ በሞራሉ ፤ በፍልስፍናው . . . ሁሉ በበዝባዥና በተበዝባዥ መሀከል ያለው ግጭት ይታያል ማለት ነው ። እንደዚሁም ደግሞ በመሠረት ደረጃ በዝባዥ የሆነው መደብ ባልባሱ ደረጃ የራሱን አስተሳሰብና ድርጅቶች በኅብረተሰቡ ላይ ያነግሣል ።

የበዝባዦች ብዝበዛና የሚነዙት አስተሳሰብ፤ የሚያቋቁሙት ድርጅት በኅብረተሰቡ ይነግሳል ። ስለተባለ ግን ተበዝባዦች ጨርሰው አሜን ብለው ተገኝተዋል ማለት አይደለም ። የገዥውን መደብ ለመቋቋም በኢኮኖሚ ብቻ ሳይሆን በየመስኩ ትግል ያደርጋሉ ።

እንደዚህ ስለተባለ አንዳንድ ነገሮች መጠንቀቅ ያስፈልጋል ። ፩ኛ/ የኅብረተሰቡ «መሠረት» በዚያ ኅብረተሰብ ውስጥ ያሉትን አስተሳሰቦችና እምነቶች ይወስናል ፤ ልባሱ የመሠረቱ ተቀጥላ ነው ስለተባለ ልባሱ መልሶ መሠረቱ ላይ ተጽእኖ አያደርግም ማለት ስሕተት ነው ። ከሁለቱ ማለትም ከመሠረቱና ከልባሱ ይበልጥ ወሳኝ የሆነ ሚና የሚጫወተው የኢኮኖሚው መዋቅር ቢሆንም በኅብረተሰቡ ውስጥ ያለው የሰዎች አስተሳሰብና ትግል የኢኮኖሚ መዋቅሩን መለወጥ ሊያዘገየው ወይም ሊያፋጥነው ይችላል ። ይህ ራሱ ከመደቦች ትግል መቀዝቀዝ ወይም መፋፋም ጋር የተያያዘ ጉዳይ ስለሆነ መደቦችና የመደቦች ትግል በሚለው ምዕራፍ እንመለከተዋለን ።

በዚሁ አንፃር ደግሞ ሁሉም የሰዎች አስተሳሰብ ራሱ የኅብረተሰቡ ኢኮኖሚ ነጸብራቅ ነው፤ የታሪክ ርምጃ ሳይንሳዊ የሆኑ የማይቀሩ ሕጎች ይከተላል ፤ ስለተባለ ሰዎች በታሪክ ውስጥ

ምንም ሚና የላቸውም ማለት አይደለም ። የታሪክን ርምጃ ሕጎች ፤ ለውጥን የሚያመጣው የሰዎች ትግልና ድፍረት ነው ። በዚህ ትግል ውስጥ ወሳኝ የሆኑ ተሳታፊ የምርቱ አመንጭ ፤ የኢኮኖሚው አንቀሳቃሽ የሆነው ሠራተኛው ሰፊ ሕዝብ ነው ። ከፍ ብለን እንዳየነው ዞሮ ዞሮ የታሪክ አንቀሳቃሽ ዋና ኃይል የምርት ኃይሎች መንቀሳቀሻ ማደግ ነው ። የምርት ኃይሎችን የሚያዳብረውና ምርት የሚያሳድገው ደግሞ ሠራተኛው ሕዝብ ነው ። ስለዚህ ሠራተኛው ሕዝብ እውነተኛው የታሪክ ባለቤት ነው ማለት ነው ።

ሠራተኛው ሕዝብ የታሪክ ባለቤትና ፈጣሪ ነው የሚባለው ሠርቶ የሚያመርተውና በማይታክት ፤ ዕረፍትን በማያውቅ ልፋት ከቀን ቀን ከዓመት ዓመት ለኅብረተሰቡ ጽኑ መሠረት የሚሰጠው እሱ በመሆኑ ብቻ አይደለም ። ከዚህም በተጨማሪ ሠርቶ ከማምረትም በላይ ኅብረተሰቡን ለመለወጥና የተሻለ ቀን ለማምጣት በሚደረገው ትግልና ወሳኝ የሆነው ኃይል የሰፊው ሕዝብ ኃይል በመሆኑም ነው ። የባርያ ሥርዓት ሲደመሰስ የትግሉ ምሰሶ የነበረው የተበዝባዥ ባርያ ኃይል ነበር ። የፊውዳል ሥርዓት ሲደመሰስ እንደዚሁ የትግሉ ምሰሶ ዋና ኃይል የጢሰኛው መደብ መሆኑ ግልጽ ነው ።

ግለሰቦችስ ታዲያ ? የከበርቴዎች አንድ ማወናበጃቸው ማርክሲዝም በኅብረተሰቡ ኢኮኖሚ ላይ ስለሚያተኩር የግለሰቦች ቅንነት ወይም ጠማማነት ፤ ጀግንነት ወይም ፈሪነት ፤ ወላዋይነት ወይም ቆራጥነት በጠቅላላው የነሱ ስሜት በታሪክ ውስጥ ፈጽሞ ቦታ የለውም ። የሚል ያስመስላል ። ይህ ግን ፈጽሞ ከእውነት የራቀ ነው ። ማርክሲዝም በታሪክ ውስጥ የግለሰቦችን ቦታ ጠቁሞ ልካቸውን ያሳያል እንጂ ግለሰቦችና መሪዎች ፈጽሞ ቦታ የሌላቸው ናቸው አይልም ።

እርግጥ ታሪክን የሚያራምደው የሠራተኛው ሕዝብ ትግል ነው ። ግን በዚህ በመደቦች ትግል መልክ በሚራመደው ታሪክ እያንዳንዱ መደብ የራሱ ፈላስፎች ፤ ግንባር ቀደም ታጋዮች ፤ መሪዎች ያንቀሳቅሱታል ፤ ለትግልም ያስፋፉታል ። ሌኒን እንዳለው « ከመሀሉ የፖለቲካ መሪዎችና ትግሉን አቀነባብረው መምራት የሚችሉ ግንባር ቀደም ወኪሎች ሳያገኝ የበላይነቱን ያጸደቀ መደብ በታሪክ ፈጽሞ አልታየም ። »

---

## ደ ብ ዳ ቤ ዎ ች

ከ፩ኛው ገጽ የዞረ

ሳለ ለባዕድ ቋንቋ በቀን ሁለት የፕሮግራም ጊዜ ከመስጠት ለአንድ ኢትዮጵያዊ ቋንቋ አንደኛው ክፍለ ጊዜ አሁኑኑ ለምን አይለቀቅም ? ከአገር ውስጥም የሱማሊኛ ቋንቋ በቀን ሁለቴ ይተላለፋል ። የኦሮሞኛ የትግሬ ቋንቋዎችም በሁለት ሬዲዮ ጣቢያዎች ይተላለፋሉ ። ይህንንም መቃወሚ ሳይሆን ለሌሎችም ዕድል ይሰጥ ለማለት ያሀል ነው ። ቅድሚያ የሚሰጠው የቋንቋው ስፋት እየታየ ከሆነ ለወላይታ ለሲዳማ ፤ ለሐዲያና ለጉራጌ ቋንቋዎች በቀን የሩብ ሰዓት ፕሮግራም እንኳን ለምን አይኖራቸውም ? በተለይም የወላይታን ቋንቋ ከአራት ሚሊዮን ሕዝብ በላይ ስለሚናገር ከአገሪቱ ሰፋፊ ቋንቋዎች አንዱ ነው ። የባህል ፤ የወጣቶችና የስፖርት ሚኒስቴርም ከየብሔረሰቡ የባህል ተጫዋቾችን ለቲያትር ቤት ቢመለምል ከፍልስፍናችን ጋር ተስማሚ ሳይሆን አይቀርም እላለሁ።

መንገሻ አደሎ

ከአርባ ምንጭ ወባ መቆጣጠሪያ እ.ኢ.

የብሔረሰቦችን እኩልነት ማረጋገጥ ባህላቸውን ማስፋፋትና ማስከበር የአዲሱ ዲሞክራቲክ አብዮታችን አንዱ ትልቅ ዓላማ ነው ። በመሆኑም በአብዮታችን ሂደት አንተ ከላይ የገለጽካቸውን ድሎች እንዳገኘን ሁሉ የቀሩትንም ብሔረሰቦች ቋንቋዎች የምናዳብርበትና ባህላቸውን የምናስፋፋበት ደረጃ ላይ እንደምንደርስ አያጠራጥርም። የአዲሱ ዲሞክራቲክ አብዮት ፕሮግራም ካስፈራቸው ትልቅ ነጥቦች አንዱ የብሔረሰቦችን ጉዳይ የሚጠቅሰው ነው ። በተለይም አብዮታችን የራስን በራስ ማስተዳደር (ሪጂናል አውቶኖሚን ) መብት ማስከበር ደረጃ ላይ ሲደርስ አሁን አንተ። የምትጠይቀው ሁሉ መልስ ያገኛል ይህ ሁሉ ሊሆን የሚችለው ግን በትግል ነውና።በትግላችን ላይ በርትተን ጠላቶቻችንን ድል እንምታቸው ።